<u>*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን*</u>

መልከአ ቅዱስ ያሬድ ካህን ወማኅሌታይ

1) *ሰላም ለዝክረ ስምከ፣*

መጠራቱ ማር ለሆነ ለስምህ መታሰቢያ፤ ሰላምታ ይገበዋል፣ እንደ የጌዴዎን ነጭ ሐር ነጭ፣ ለሆነ የራስህ ጠጉር ፣ሰላምታ ይገበዋል፣ ያማረ መዝሙርን የምትናገር ፣ዘማሪ *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ባሕር ቀለምን ቢሆን ደጋም ፣ሸምበቆ ቢሆን ያንተ ክብር በመጻፍ አያልቅም።

2) *ሰላም ለሥዕርተ ርእስከ፣*

የካህናት አክሊል ለተሸከመ ራስህ፤ ሰላምታ ይገበዋል። የተደነቀ ጸሀይ ለበራ ፊትህም ፣ ሰላምታ ይገበዋል። *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* በመላእክት ዘንድ የተነገረ የማሕሌት ድምጽ ዘወትር በአፋቸው ላዳመጹት፣ ከወንጌል ካህናት ነጎድጓድን ያነዋውጣል ምድርንም ያንቀጠቅጣል።



3) *ሰላም ለቀራንብቲከ፣*

ኩልን ላልወደዱ ቅንድቦችህ ፣ሰላምታ ይገባቸዋል፣ ወደ ላይ ለሚያንጋጥጡ ፣ አይኖችህም ፣ሰላምታ ይገባቸዋል። *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ለመጽሐፍ ትምህርት ኃያል ባላገኝህ በዝቡ ትጋት ከመጽሐፍ ውስጥ፣ እንደተባለ ከዕንጨት ላይ የትል፣ መውጣት አብነት ሆነህ።

4) *ሰላም ለአዕዛኒከ፣*

የሱራፌ ማኅሌትን ለሰሙ ጆሮችህ፣ ሰላምታ ይገባቸዋል። የውስጥና የደጅ ደምግባት ያላቸው ጉንጮችህ፣ ሰላምታ ይገባቸዋል። *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ከአፍህ የወጣ ጣፋጭ ምስጋና ቀድሞ ከአለም መካከል ቢሰራ መላእክትን ያስደስታል ሰውም ያስደንቃል።

5) *ሰላም ለአዕናፊከ፣*

ፈጽሞ አለ መጉደል ለአፍንጮችህ ፣ሰላምታ ይገበቸዋል፣ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ማኅሌት ለተናገሩ ከንፈሮችህም ፣ሰላምታ ይገባቸዋል። ሥጋን የምትቀጣ በደልን የምታቀል፣ *የካህናት አለቃ ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ተሰብስበው አንተን የሚያመሰግኑ በበጎ፣ ጸጋህ ጸጋን፣ አያጡም።

6) *ሰላም ለአፉከ፣*

ከስድብ ነገር ለተከለከለ አፍህ፣ ሰላምታ ይገበዋል። የጋለሞታን ሳቅን ነውረን ላላደረጉ ጥርሶችህ፣ ሰላምታ ይገባቸዋል። *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* የምስጋና ጨው በብዙ፣ ድካም ፣ እጅግ አልጫን ከመሆን አለምን አጣፍጣት።

7) *ሰላም ለልሳንከ፣*

ፈጣሪን ላመሰገኑ አንደበትህ ፣ ሰላምታ ይገበዋል። የዝማሬ ጣፋጭነትን ለተናገረ ቃልህም ፣ ሰላምታ ይገበዋል ። *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ያንድነትና የሦስትነት ቄስ አንተ ነህና፣ ከሁሉ ትርጓሜ ልብሱ፣ ግምጃ የሆነ፣ የካህናት አለቃ አሮን አይተካከልህም።

8) *ሰላም ፣ እብል፣ ለእስትንፋስከ፣*

ላማረ እስትንፋስህ፣ ሰላምታ ይገበዋል ፣ ያማረ ዝማሬ ደጃፍ ለሆነ ጉሮሮህም፣ ሰላምታ ይገበዋል። ያምረ ልብ ስም የለበስክ፣ *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ወይን ማጎሌት ለመጠጣት በተቀዳ ጊዜ ከአዲስ አዳራሽ መታዘዝ፣ ውስጥ ፍጹም አለም ከመሆን ጎዘን ይረሳል።

9) *ሰላም ለክሳድከ፣*

ከልኩ ላልደነደነ አንገትህ፣ ሰላምታ ይገበዋል፣ ዳግመኛም ለትክሻህ፣ ሰላምታ ይገበዋል። የሱራፌ ማኅሌትን ትማር ዘንድ እንደተጻፈ፣ *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ዘወትር ለፈጣሪህ ሦስት ከወፎች ላከልህ።

10) *ሰላም ለዘባንከ፣*

በክብር ለተነደፈ ጫንቃህ፣ ሰላምታ ይገበዋል፣ የእውቀት ስጦታ ላደረበት ደረትህ፣ ሰላምታ ይገበዋል፣ *ቅዱስ ያሬድ ሆይ*

ምስጋናን ስትጀምር የጽዮን ፊተኛ አምላክ ምድርን ፈጠረ ፣ትላለህ ለሙሴም የሚሰራው ፣ሥራን አሳየን ትላለህ።

11) *ሰላም ለሕጽንከ፣*

ተቀማጭ ጽድቅን ላሰቀመጠ ብብትህ፣ ሰላምታ ይገበዋል ። ዝማሜን ላሳመሩ እጆችህም፣ ሰላምታ ይገባቸዋል። ሽታ ክህነትን ምሽተትክ መምህር፣ *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ቀጠሮን የረቀቀ ትርጓሜ ዘመን ልጆች ቀጠሮን ሳንጠብቅ በመዓዛህ እንሮጣለን።

12) *ሰላም ለመዛርዒከ፣*

ማሸነፍ ብርታትን ለተሞሉ ከንዶችህ፣ ሰላምታ ይገባቸዋል። ዳግመኛም የጠላት ኃይልን ለመታ፣ ጥንቻህ፣ ሰላምታ ይገበዋል ። *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ትንሽ ማኅሌትን በአለም እርሻ የምትዘራ ነህ ከቃልህ ድምጽ የሚሰማ፣ ያደንቃል የሚያይ የሰው አይንም ዳግመኛም ይደነቃል።

13) *ሰላም እመትከ፣*

የፍጹም ጸጋ ከንድ ለሆነ ከንድህ ፣ሰላምታ ይገበዋል። የጣፋጭ ማኅሌት ጸናጽልን ለያዘ ማሃል እጅህም ፣ ሰላምታ ይገበዋል። የእሳታውያን መላእክት ዝማሬ የትክሻ ልብስ የሆነህ፣ *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ወደ ወንጌላዊ ገዳም በመግባትህ ፣ጊዜ ክህነት ሥራህ የተነሳ አለም ትደሰታለች።

14) *ሰላም ለአጻብዒከ፣*

የማኅሌት መዝሙርን ለጻፉ ጣቶችህ ፣ ሰላምታ ይገባቸዋል። ከበርዶ ጋራ አንድ ለሆኑ የነጩ ጥፍሮችህ፣ ሰላምታ ይገባቸዋል። *ቄስ ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ከአለም ፍቅርህ ዳርቻ ውስጥ ሰው ቢቆም እልፍ ከተባለ አምላክ ዘንድ ፣ክብርን ያገኛል ተስፋም ያገኛል።

15) *ሰላም ለገቦከ፣*

በእንቅልፍ ጊዜ ለማይተኝን ጎንህ፣ ሰላምታ ይገበዋል። የዚህ አለም መብልን ላልተሸከመ ሆድህም፣ ሰላምታ ይገበዋል። *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* በገዳም ጥናት አምልሃለሁ ምግቤን በየቀኑ ዛሬ ፣ትሰጠኝ ዘንድ፣ የቀድሞና የዛሬ በደሌን ትተው ዘንድ።

16) *ሰላም ለልብከ፣*

ጥበብን ላበዛ ልብህ፣ ሰላምታ ይገበዋል። ዳግመኛም ለኩላሊትህ፣ ሰላምታ ይገበዋል። *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* አንቀጸ ብርሃንን መናገርን በጀመርክ ጊዜ የጸጋ ውሃን የታጠበ እግርህ በአክሱም መቅደስ፣ አንድ ክንድ ያህል ከመሬት ከፍ ብሎ ተገኘ።

17) *ሰላም ለሕሊናከ፣*

የከንቱ ነገርን ለማያስብ አዕምሮህን፣ ሰላምታ ይገበዋል። በመንፈስ ቅዱስ እሳት በተቃጠለ አንጀትህም፣ ሰላምታ ይገበዋል። *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ከገብረ መስቀል ደስተኛ መንግሥት ከመነንክ በኋላ የመጋደልህ፣ ገዳም ሰሜን ማስፈራት አላስፈራህም እሱ የደጋ ምድር ሳለ የውስጡም በረዶ ሳለ አላስፈራህም።



18) *ሰላም ለንዋየ ውስጥከ፣*

በመልአክ እጅ ለተጠበቀ የሆድህ ዕቃ፣ ሰላምታ ይገበዋል። ከሆድ ውስጥ ለረጠበ እንብርትህም ዳግመኛ፣ ሰላምታ ይገበዋል። የድንቅ ዝማሬ ቄስ አንተ፣ *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* በአንድ አምላክ ፈቃድ ምሶሶቿን ስታቁም ጥበብ ለራሷ ማደርያን ሰራች።

19) *ሰላም እብል ለሐቋከ፣*

በመጥራት ለጎንህ፣ ሰላምታ ይገበዋል፣ እላለሁ በማማለድና የጸሎት ምሰሶች ጫኖችህም፣ ሰላምታ ይገበዋል፣ *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* የዝማሬህ ጣዕምን መዳመጥን ሲያዳምጥ ገብረ መስቀል በሚጠናው ፣ የብረት ዘንግ እግርህን ፣በወጋው ጊዜ አልታወቀህም።

20) *ሰላም ለአብራኪከ፣*

የአምላክ ስግደት ለማይንቁ ጉልበቶችህ፣ ሰላምታ ይገባቸዋል። በጠና በቀኖና ቦታ ለቆሙ እግሮችህም፣ ሰላምታ ይገባቸዋል። *የጨለማ አለም ብርሃን የሆንክ ቅዱስ ያሬድ ጸሐይ ሆይ* ከብዙ ጎደና ጉም በደልና አበሳ ደመና መሸሸግ አልቻሉም።



21) *ሰላም ለሰኳንዊከ፣*

ጎደና ስሕተት ለማይድጡ ተረከዞችህ፣ ሰላምታ ይገባቸዋል። የበለጠን ለበቀሉ መኸጃህም፣ ሰላምታ ይገባቸዋል። *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ድምጽዋ ድንቅ የሆነች ዝማሬህ ልጆች ፣በዕልልታ ቃል ተባብረው ፣ በጊደር መዝለል ዘለሉ እንደ አሸዋ በዝተዋልና።

22) *ሰላም እብል ለአጻብዓ፣ እግርከ ክልኤ*

ከላያቸው ጥፍሮችህ ላላቸው፣ የሁለት እግሮችህ ጣቶች፣ ሰላምታ ይገባቸዋል፣ እላለሁ፣ *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* የመንፈሳዊ ስራህ ደምግባት ተወደደ ከአለም፣ ልጆች በጧትና በማታ በብዙ ፣መጋደል አንተን የመሰለ የለም።

23) *ሰላም ለቆምከ፣*

የተመረጠ ዛፍን የመሰለ ቁመትህ፣ ሰላምታ ይገበዋል፣ ላማረ መልክህም ዳግመኛ፣ ሰላምታ ይገበዋል፣ *ወርቅ ልብሱን የለበስክ ቄስ ቅዱስ ያሬድ ሆይ* ከፍ ባለች የወንጌል ድንኳን በጌታህ እንዴት ትወደዳለህ አምላክ ፊት፣ ምስጋናን ስታመሰግን።

24) *ሰላም ለጸአተ ነፍስከ፣*

ከከበረ ሥጋ አዳራሽ ለነፍስህ መውጣት፣ ሰላምታ ይገበዋል፣ አስደናቂ ሽታን ለሞላ አስከሬንህም፣ ሰላምታ ይገበዋል፣ *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* በሥልጣንህ ባሕር ውሃ እጠበኝ ከነዚህ ዕድፎች በደልና ኃጢአት ፣እንደ ጴጥሮስ መምህር ማንጣት አለህና።

25) *ሰላም ለግንዘተ ሥጋከ፣*

መዋች ብልሃተኛ ላልሆናት የሥጋህ መግነዝ፣ ሰላምታ ይገባታል፣ ተማራማሪ ለማያገኛት የተሸሸገች መቃብርህም፣ ሰላምታ ይገባታል፣ *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* የሥጋህ መቃብር የበረዶ ቦታ ናት ሁለት አለሞችን ፣የሚገዛ እግዚአብሔር ንጉሥ፣ ያች ምዕራፍህ ናት ብሎሃል።

26) *መዝሙረ ማኅሌት፣*

የዘመነ በልግና የማዕረር የበጋና የክረምት ጣፋጭ፣ መዝሙርን የሠራህ የማርያም ምስጋና፣ *ቄስ ቅዱስ ያሬድ ሆይ* የጠራ ብሩርና የወርቅ ያልደለ፣ የረዘመ ሰማይ ገንዘብ ጽድቅን አቤቱ አዘጋጅልን።



27) *መዝሙረ አምላክ ሕያው፣*

የተባረከች ወላዲቱና የሚኖር አምላክ መዝሙርን የተጉ ፣የነቢያት የሐዋርያት፣ የጻድቃንና፣ የሰማዕት፣ የደናግልና፣ የመነኮሳት፣ የካህናትና፣የዲያቆናት፣ ምስጋና የተናገርክ፣ *ቅዱስ ያሬድ ሆይ* በምስጋናም የጻፍክ የስምህ መታሰቢያ ከሞት አዳኝ ይሁነኝ።

28) *አ አምላክ ቅዱስ ያሬድ*

***የቅዱስ የያሬድ አምላክ ሆይ* ከሥጋና ከነፍስ መከራ ፈጽመህ አድነኝ ለዘለዓለሙ አሜን።**

